


# የቴምብር ቀረጥ አስተዳደር ሥልጠና

## ሞጁል 7

ገቢዎች ሚኒስቴር

የካቲት 2018



# ይዘት

- መግቢያ
- ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ ሁኔታ
- ክፍል ሁለት፡- የቴምብር ቀረጥ  አሰራር  ሥርዓት
- ክፍል ሶስት፡-የቴምብር ቀረጥ አስተዳዳራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች
- ማጠቃለያ
- ማጣቀሻ

# መግቢያ

- በዓለም አቀፍ ደረጃ የቴምብር ቀረጥ ክፍያ እ.ኤ.አ. በ1694 እንደተጀመረ መረጃዎች እንደሚያመለካከቱ፤
- በ19ኛው ክፍለ ዘመን እንደ ግብይቶቹ/ዶክመንቶች ዓይነትና ዋጋ መጠን የተለያዩ መጠኔዎች ጥቅም ላይ መዋላቸው፤

# መግቢያ….

- በኢትዮጵያ የቴምብር ቀረጥ የሚጣለውና የሚሰበሰበው በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990፤ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 612/2001 እና በአዋጁ እስካልተቃረነ ድረስ በቴምብር ቀረጥ ደንብ ቁጥር 221/1954፤ ታክስ አስተዳደር 983/2008 መሆኑ፤

# ክፍል አንድ:- አጠቃላይ ሁኔታ

## 1.1. ዋና ዓላማ

ሠልጣኞቹ በቴምብር ቀረጥ ህግ ውስጥ ስለተደነገጉት የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች ፤ አተማመን ፤ አከፋፈል ፤ የክፍያ ጊዜ እና የቀረጡ አስተዳደር ሥነሥርኣቶችን ተገንዘበው መብታቸውን አስከብረው ግዴታቸውን ይወጣሉ ።



# ዝርዝር ዓላማዎች.....

ሠልጣኞች ፡

- የቴምብር ቀረጥ ጽንሰ ሃሳብንወ  ይረዳሉ።
- የቴምብር  ቀረጥ ሥለት መሰረትና  መጣኔን  ይለያሉ::
- የቴምብር ቀረጥ ዕዳ  እና የክፍያ ሁኔታን ይገልጻሉ ።
- ከቴምብር ቀረጥ ነጻ የሆኑትንና ያልሆኑትን አገልግሎቶች/ሰነዶችን ይለያሉ።
- የቴምብር ቀረጥን አለመክፈል የሚያስከትለውን አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣቶችን  ይገነዘባሉ።

# 1.2. ወሰን

## 1.2.1. ሽፋን

በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990፣ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 612/2001 እና በቴምብር ቀረጥ ደንብ ቁጥር 221/1954፣ ታክስ አስተዳደር 983 /2008 ያካትታል።

## 1.2.2. የሥልጠናው ተሳታፊዎች

ግብር ከፋይ ድርጅቶች/ማህበራት፣ሥራ ኃላፊዎቻቸው እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተቀጣሪዎች፣ የታክስ እንደራሴዎች እንዲሁም ታክስ ወኪሎች የሚሠለጥኑ ይሆናል።

## 1.2.3. ስልጠናው የሚወስደው ጊዜ ፡

2 ሰዓት



## 1.3. ትርጉም

- **ሰነድ** ማለት ማናቸውም መብት ወይም ግዴታ የተመሰረተበት፤ የተላለፈበት፤ የተወገደበት፤ልኩ የተወሰነበት ወይም የተስፋፋበት ወይም የተጠቀሰው ድርጊት ተፈጽሟል የተባለበት ማንኛውም ጹሁፍ ነው ።
- **ግልግል (Award)** ስለ ዕርቅ፤ ስለ ስምምነት ወይም ስለ ሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ በሁለት ተዋዋይ ወገኖች የተደረገ ስምምነት
- **ማገቻ (Notarial acts/bonds)** የተወሰነ ነገር በመፈጸሙ ወይም ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚቀር ሆኖ

# ትርጉም….

አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውንም ሰነድ ………..

- **ሰነድ ማስፈጸም** ማለት ሰነድ መሥራት ፣ ማውጣት ፣ በሰነዱ የተመለከተው ማስፈጸም …..



# ክፍል ሁለት
# የቴምብር ቀረጥ አስራር ሥርዓት

## 2.1. የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች

- የማንኛውም ንግድ ማህበር፤ የህብረት ሥራ ማህበር ወይም የማንኛውም ዓይነት ማህበር መመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ
- ግልግል (Award)
- ማገቻ (bonds)
- የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ
- ውል ፤ ስምምነትና የእነዚህ መግለጫ
- የመያዣ ሰነዶች
- የህብረት ስምምነት
- የሥራ (የቅጥር) ውል .......

# አስተዳደር ........



# 2.2. የቴምበር ቀረጥ ታሪፍ

| ተ.ቁ. | የሠነዱ ዓይነት | የተወሰደ ስሌት መሠረት | የማሰከፊያ ልክ |
|---|---|---|---|
| 1 | የማንኛውም የንግድ ሥራ ወይም ማናቸውም ሌላ ማህበር የተመሰረተበት መተዳደሪያ ደንብ<br>ሀ/ መጀመሪያ ሲፈጸም<br>ለ/ በመለጠቅ ሲፈጸም | በቁርጥ<br>" | ብር 350<br>ብር 100 |
| 2 | የህብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ<br>ሀ/መጀመሪያ ሲፈጸም<br>ለ/ በመለጠቅ ሲፈጸም | በቁርጥ<br>" | ብር 35.0<br>ብር 10.0 |
| 3 | ግልግል | በዋጋው | የሚተመን 1%<br>የማይተመን ብር 35 .00 |

# ታሪፍ ....

| | | | |
|---|---|---|---|
| **4.** | **የዕቃ መከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ** | **በዋጋው** | **1%** |
| 5 | ውሎች፣ ስምምነቶች፣ መግለጫዎቻቸው | በቁጥር | ብር 5.00 |
| 6 | የመያዣ ሰነድ | በዋጋው | 1% |
| 7 | የህብረት ሥራ ስምምነት<br>ሀ/ሲመዘገብ<br>ለ/ሲሻሻል | በቁርጥ<br>" | ብር 350.00<br>ብር 100.00 |
| 8 | የቅጥር ውል ስምምነት | የአንድ ወር ደመወዝ | 1% |
| 9 | ኪራይ፣ የተከራይ አከራይና መሰል መብት ማስተላለፍ ሰነድ | በዋጋው | 0.5% |

# ታሪፍ ....

| 10 | ማረጋገጫ | በቁርጥ | ብር 5.00 |
|---|---|---|---|
| 11 | የውክልና ሥልጣን | በቁርጥ | ብር 35 .00 |
| 12 | የንብረት ባለቤትነት ሥም ማስመዝገቢያ | በዋጋው | 2 % |
| 13 | የውክልና ሥልጣን | በቁርጥ | ብር 35 .00 .... |

# ታሪፍ



# 2.3. የቀረጡ አተማመን

- በዋጋው መቶኛ/በቁርጥ
- አንድ ሰነድ ላይ ተከፋዩ የሚሆነው ቀረጥ በብር ሳይሆን በሌላ ገንዘብ ከሆነ፤ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው የምንዛሪ ልክ ነው።
- በስቶክ ወይም ሌላ ዋስትና ባለው ነገር ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዋጋው ላይ ተመስርቶ ከሆነ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው አማካኝ ዋጋ መሠረት፤
- ብዙ የተለያዩ ነገሮች የተጠቃለሉበት ወይም ለብዙ ልዩ ሰነዶች የቆመ ማናቸውም ሰነድ በያዛቸው ልዩ ልዩ ሰነዶች መጠን በእያዳንዱ ሰነድ ላይ የሚከፈለው ቀረጥ በመጠቃለል ተደምሮ ይከፈልበታል።

# የቀረጡ ....

- ንብረቱን በባለቤትነት ለማስመዝገብ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የሚተመነው የንብረት ዋጋ ላይ ሆኖ ዋጋው በታክስ ባለሥልጣን ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ሲሆን ተቀባይነት ካላገኘ ግን ተገቢው የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት የንብረት ዋጋ ሥልጣን ባለው አካል እንዲተመን ይደረጋል፡፡

## የሰነዱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው

- በኢትዮጵያ ውስጥ ሰነዱን የሚሠረው ወይም የሚሰጠው ሰው ሰነዱ እንደተፈጸመ ቀረጡን የመክፍል ግዴታ አለበት፡፡
- በኪራይ ውል ውስጥ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ተከራይ ቀረጡን ይከፍላል፡፡
- በንብረት በለቤትነት ሥም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የቴምብር ቀረጥ ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የመክፈል ግዴታ ያለበት የንብረት ባለቤትነት የሚመዘገብለት ሰው ይሆናል፡፡
- ውል ወይም ስምምነት የሚመሰረቱ ወገኖች ለቴምብሩ ቀረጥ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

# አካላት…

- **በሥራ/ቅጥር ውል** ላይ የሚከፈለውን ቀረጥ የመክፈል ግዴታ የአሠሪው ይሆናል፡፡
- **ጉዳያቸውን በግልግል** የሚያስወስኑ ወገኖች እና በህብረት ስምምነት ላይ ለሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ አከፋፈል በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
- በህብረት ስምምነት ላይ ለሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ አሠሪውና ሠራተኞቹ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ ፡፡

# 2.5. ቀረጡ የሚከፈልበት ጊዜና ሁኔታ

## 2.5.1. የክፍያ ጊዜ

- በመመሠረቻና መተዳደሪያ ጸሑፎች ከምዝገባ በፊት ወይም በምዝገባ ጊዜ፤
- በግልግል ውሳኔው ከመስጠቱ በፊት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ፤
- በውል ወይም በስምምነት ሰነዶች ላይ ከመፈረማቸው በፊት ወይም በሚፈረሙበት ጊዜ፤
- ኪራይ ወይም በተከራይ አከራይ ውል ላይ ውሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈርሙበት ጊዜ
- በማረጋገጫ ሰነድ ላይ ማረጋገጫው በሚሰጥበት ጊዜ፤
- በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ የማስመዝገቡ ተግባር ከመፈጸሙ ወይም በሚፈጸምበት ጊዜ

# 2.5.2. የክፍያ ሁኔታ

- የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር 50.00 በታች በሚሆንበት ጊዜ ክፍያ ተገቢውን ዋጋ የያዘውን ቴምብር በመለጠፍ ይፈጸማል፡፡
- የሰነዱ ዓይነትና ሁኔታ ለየት ያለ አሠራርን ሲጠይቅ የታክስ ባለሥልጣኑበሚሰጠው አቅጣጫ/መመሪያ መሠረት ቴምብር ከመለጠፍ በሌላ መንገድ ቀረጡ እንዲከፈል ሊያደርግ ይችላል፡፡
- የተምብር ቀረጥ በተለጠፈበት ሰነድ የሚሠራ ወይም የሚቀበል ሰው በዚህ ቴምብር ሁለተኛ እንዳይሰራ ተደርጎ ይሠረዛል፡፡
- ቴምብሩታክስ ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሠረት ካልተሰረዘ ሰነዱ ቴምብር እንዳልተለጠፈበት ይቆጠራል፡፡

# ሁኔታ....

- የቴምብር ቀረጥ መሰብሰብና  ህጉን ማስፈጸም
- ቀረጥ ከፋዮች ስለቀረጡ አወሳሰን የሚረዱ ልዩ ልዩ ሰነዶችና ውሳኔዎችን እንዲያቀርቡ ለማድረግና ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው እራሱ ቀርቦ እንዲመርምር ወይም እንዲያስረዳ በማድረግ ውሳኔ መስጠት

# 2.6. ከቀረጡ ነጻ ስለመሆን

- በመንግስት በጀት የሚተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች፤
- የአስመጪነት የንግድ ፈቃድ ያላቸው ነጋዴዎች ለሽያጭ የሚያስመጡት ንብረት በአስመጪዎቹ ስም በሚመዘገብበት ጊዜ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልበትም፡፡
- መንግስት ባጸደቃቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ኮንቬንሽኖች መሠረት ሰነዶች ነጻ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡
- ተመሳሳይ መብት የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ኢምባሲዎችን፤ ቆንስላዎችን እና ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችን ገንዘብ ሚኒስትር ከቴምብር ቀረጥ ነጻ ሊያደርጋቸው ይችላል
- የአይክስዮን ድርሻ የምስክር ወረቀት ሲመዘገብ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልም፡፡

## ከቀረጥ ነጻ .....

ለገንዘብ ሚ/ር ጥያቄዎች ቀርቦ ከቀረጡ ነጻ እንዲሆኑ የተፈቀደ ሰነዶች

- በኢንቨስትመንትላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ብቻ ለኢንቨስትመንት የሚወስዱት ብድር ጋር በተገናኘ በመያዣ ሰነድ ላይ ከሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ነጻ እንደሆነ፤
- የካፒታል ንብረቶች ለጥቃቅንና አንስተኛ እናመካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ዕቃዎችን በዱቤ ግዥ የሚያቀርባቸው አዲስ የካፒታል ዕቃ ኪራይ ፋይናስ ንግ ሥራ አ.ማ. የካፒታል ንብረቶች በስሙ ሲመዘገብ በባለቤትነት ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ ከሚከፈለው 2% (ሁለት በመቶ) የቴምብር ቀረጥ ክፍያ ነጻ መደረጉ
- በውጭ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለሥራ ማስከኛ ከሚወስዱት ብድር ጋር ተያይዞ በመያዣ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ነጻ መደረጉ፤

## ከቀረጡ ነጻ .....

- የኢትዮጵያ ሴቶች ፌዴሬሽን ከመንግሥት የተሰጡት/ የሚሰጡ ተሽከሪካሪዎች የባለቤትነት ሥም ዝውውር ሰነድ ላይ ስለሚከፈለው ቴምብር ቀረጥ ነጻ መደረጉ፤
- የግብርና ምርትማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የማደበሪያ አቅርቦት ለአርሶ አደር ለማደል ከሚወስደው ሜርቸንዳይዝድ ብደር ጋር በተገናኘ በመያዣ ሰነድ ላይ ከሚከፈል ቴምብር ቀረጥ ነጻ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለኢንተርፕራይዞች ለሊዝ ፋይናስንግ ሥርዓት የሚያቀርባቸው ተሽከሪካሪዎች በባንኩ ንብረት ባሌበትነት ሥም ማስመዝገቢያ ቀረጥ ነጻ እንደሆኑ፤

## 3.1. ይግባኝ የማቅረብ መብት

- በታክስ/ቀረጥ ውሳኔው ላይ ቅር የተሰኘ ሰው የውሳኔው ማስወቂያ በደረሰው በ21 ቀናት ውስጥ በውሰኔው ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ በጹሑፍ ማቅረብ ይችላል
- ለበላሥልጣኑ ቅሬታ አቅርቦ በተሰጠው ታክስ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ሰው ቅጣትና የዘገየ የከፍያ ወለድ ሳይጨምር በክርክር ላይ ያለ ታክስ 50% (ሃምሳ በመቶውን) በመክፈል ለግብር ይግባኝ ኮሚሽን በ30 (በሳላሳ) ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።
- ኮሚሽኑ ባስተላለፈው ታክስ ውሳኔም ቅር ከተሰኘም የውሳኔውን 75% (ሰባ አምስት በመቶ) በመክፈል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

## የቴምብር ቀረጥ….

### 3.2. አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣት

- ማንኛውም የቴምበር ቀረጥ ከፋይ

- በምስክርነት ካልሆነ በስተቀር የቴምብር ቀረጥ ሊከፈልበት ሲገባ ቀረጡ ያልተከፈለበትን ሰነድ ሥራ ላይ ያዋለ ወይም የፈረመ ወይም፤
- የቴምብር ቀረጥ ላለመክፈል ወይም አነስተኛ የቴምብር ቀረጥ ለመክፈል በማሰብ የአንድን ሰነድ ትክክለኛ ባህርይ ያልገለጸ ወይም የደበቀ እንደሆነ 25000.00 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) እስከ 50000.00 ብር (ሀምሳ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከ3-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

# ቅጣት ….

- ቴምብሮቹን  ወይም ቴምብር የተመታባቸውን ሰነዶች ሳይፈቀድለት የሰጠ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ እንደሆነ  ብር 5000.00 (ብር  አምስት ሺህ ብር)  እስከ ብር  25000.00 (ሀያ አምስት ሺህ ብር)  በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከ3-5 ዓመታት በሚደርስ ጽኑ ዕሥራት ይቀጣል፡፡

# ማጠቃለያ

የቴምብር አዋጅ ቁጥር 110/1990

- በሐዋላ እና የተጻፋ ሰነዶች፤ ቼክ፤ የመድን ውል፤ የድርሻ ማረጋገጫ፤ ደረሰኝ፤ ትኬት ለመንግሥት፤ ለህዝብና ለግል ድርጅቶች ወይም ሌሎች መሰል ተቋማት በሚቀርቡ አቤቱታዎችና ማልከቻዎች አማካኝነት የሚፈጸመውን/ የሚሰበሰበውን የቴምብር ን ቀረጥ አስቀርቷል፡፡
- ይህም በተለይ የፋይናስ አገልግሎቶች አፈጻጸም እንዳይጓተትና የትብብር ሥራዎች እንዲበረታቱ የሚያግዝ እርምጃ ሲሆን ታክስም በአገልግሎት ሰጪው በተገኘውና በተመዘገበው ገቢ ላይ ተሰብስቦ ስለሚከፈል አስተዳደሩን ቀሪ አድርጓል፡፡

## የሙከራ/ክለሳ ጥያቄዎች

1. የቴምብር ቀረጥ ምንድነው?
2. የቴምብር ቀረጥ ሥለት መሰረትና መጣኔን ያብራሩ?
3. የቴምብር ቀረጥ ዕዳ እና የክፍያ ሁኔታን ይገለጹ?
4. ከቴምብር ቀረጥ ነጻ የሆኑትንና ያልሆኑትን አገልግሎቶች/ ሰነዶችን ምሳሌዎችን ይጥቀሱ?
5. የቴምብር ቀረጥን አለመክፈል የሚየስከትለውን አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣቶችን ይግለጹ?

# ማጣቀሻ ፣

- ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣ አዋጅ ቁጥር 110/1990 እና የቴምብር ቀረጥ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅቁጥር 612/2001
- የቴምብር ቀረጥ ደንብ ቁጥር 221/1954
- የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008
- ከቴምብር ቀረጥ ጋር ተያይዞ በተለያዩ ጊዜያት የተላለፉ ሰርኩላሮች
- በሚ/ር መ/ቤቱ በታክስ ህጎች ላይ የተዘጋጁ የሥልጠና ማኗሎች

# ቴምብር


POSTAGE
POSTAGE 3D
POSTAGE 4D
POSTAGE 4D
POSTAGE 4D
POSTAGE 5D

# አመሰግናለሁ!

Email: morethiopia@gmail.com